# መግለጫ

## (ት.ህ.ነ.አ.ድ)

## የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት

የመጀመሪያ እትም

በየካቲት ወር 1968 ዓ/ም

## ማውጫ


መቅድም ........ V

መግቢያ ........ VIII

I እሁን ያለው ሁኔታ

1- ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ........ 1

ሀ. ፖለቲካዊ ስልጣን ........

ለ. የፖለቲካ ነፃነት አከባበር ........ 5

ሐ. ብሄራዊ ተፅእኖ ........ 7

መ. ፕሮፓጋንዳ ........ 10

2- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ........ 12

ሀ. የመሬት ይዞታው ስርዓትና ችግሩ ........

ለ. የኢንዱስትሪዎች አከመስፋፈት ........ 13

3- ማኅበረተሰባዊ ሁኔታዎች ........ 14

ሀ. ራስን መጣል [ዲ·ሁማናይዜሽን] ........

ለ. የማኅበረተሰቡ ወደ ኋላ መቅረትና አርአያ ማጣት 15

II መፍትሔው

ሀ. ብሔራዊ ትግል ........ 17

ለ. የትጥቅ ትግል ........ 21


III


III. አካባቢ ለሆኑት ውስጣዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ ያለን አቋም ........

1. የመሬት ጉዳይ ........ 22

2. የከተማ ቦታና የገጠር ቤቶች ጉዳይ ........ 30

3. የኤርትራ ጉዳይ ........ 32

4. የኢንዱስትሪ ንብረት ........ 34

5. ኢምፔሪያሊዝምና ስለሶስተኛው ዓለም ........ 36

6. የውጭ ጉዳይ አመራር ........ 37


IV

# መቅድም

ይህ መፅሐፍ የትግራይ ሕዝብ ሃቀኛ ወኪል የሆነው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት [ተ.ሓ.ህ.ት]* መግለጫና የትግሉ መመሪያ ነው። የትግራይ ሕዝብ ማለት በትግራይ ውስጥ የሚኖሩትንና ለተለያዩ ምክንያት ከትግራይ መሬት ውጭ የሚኖሩትን ሕዝቦች በሙሉ ያጠቃለለ ነው። [ትግሬኛ ተናጋሪዎች፣ ኣፋር (ጠለጣለ)፣ አገው፣ ሳሆ፣ ኩናማ፣ ወ.ዘ.ተ.] የትግራይ መሬት በደቡብ ኣካውና፣ በሰሜን መረብ ሊያገለሉት በምዕራብ በኩል ደግሞ ወልቃይትንና ፀገዴን ያጠቃልላል።

ትግራይ** አክሱም እስከወደቀችበት ጊዜ ድረስ የአክሱም መንግሥት እየተገዛች ትጠራ ነበር። አክሱም ከወደቀች በኋላም እራሷን በማስተዳደር ከብዙ ጊዜ በኋላም ቆላ አልፎ አልፎ ጎንደር ከነበሩት ነገሥታት ግብር መክፈሏ አልቀረም።

በአፄ ዮሐንስ ዘመን መንግሥት ኃይሏ በርትቶ በጎንደር የነበሩትን ነገሥታት በቁጥጥሯ ሥር አውላ ነበር፤ ይሁን እንጂ አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ በዳግማዊ ምኒልክ ትምክህተኛ ትግራይ በሸዋ ማእከላዊ ግዛት ሥር ወደቀች። ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው የአማራው የመሳፍንት ሉዶንና ተከታዮች የትግራይን ነፃነት ገፈው የሕዝቧን እንድትገዛ ያደረጓት። ግለኛና ሰውር በሆነ ዘዴዎቻቸውም [አዋጅ ዘዴዎች] የትግራይ ሕዝብ በድንቁርና፣ በበሽታ፣ በረሃብ አዘቅት ውስጥ እንዲሰምጥ ያደረጉት። በተለይም ትግሬነቱን በፍርሃት እንዲጠላና ቋንቋውን በግድ አማራ ለማድረግ ያለምክንያት ዘዴ ገድሮም መሬቱ ተቆርሶ ለከተወለደበትና የተደረገበ ጭቆና ለሚደርስበት አገሩን ጥሎ ተሰደደ። ባጠቃላይ ባለፉ ጊዜ ትግራይ ነፃነቷ የተገፈፈች፣ መሬቷ ተቆራርሶ የተወሰደባትና የተወሰሰ ችግር የደቀቀው ሕዝብ የሚኖርባት ጭቆና ባሕር ናት።



* ተ.ሓ.ህ.ት. ግልጽ ፖለቲካዊ ማነቃቃትና አሰራትም ንቅናቄ በትግራይ ምድር ማካሄድ የጀመረበት ከየካቲት ወር 1967 ዓ.ም ወዲህ ሲሆን ቆሎ ከዛ በፊት የነበረ ትግራይ ተማሪዎች ድርጅት (ብ.ት.ተ.ድ.) በሚል ስም ከለይኩት ወራት የሆነ ምስጢራዊ ድርጅቶችና ለድርጅቱ መዘጋጀትን አድርጓል። ይሁን እንጂ ተ.ሓ.ህ.ት በዚህ ጊዜ

ብቻ የተፈጠረ ተቋምነቱም ቀጠለ ሳይሆን፡-

(ሀ) ጭቁኑ የትግራይ ሕዝብ ከሰማንያ (80) ዓመት በላይ ትግል ባደገ ያፈራው ፍሬ –

(ለ) ተራማጅ ትግሉ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ ፀንሶት የነበረውን እንጉቴ ልጅ ነው::

** ስለ ጊዜ ትክክለኛ የትግራይን ታሪክ ለማወቅ "የትግራይ ታሪክ፣ መሬትና ሕዝቧ" በሚል ርዕስ ተ.ሓ.ሕ.ት. ያዘጋጀውን መጽሐፍ መመልከት ይጠቅማል:: –

—Yox—



# መግቢያ

የመደብ ብዝበዛና ብሔራዊ ጭቆና በሶሺያሊስት ሥርዓት ንቁና ተራማጅ የሆኑ ሁሉ ከተጨቋኙ ሰፊ ሕዝብ ጋር ሆነው ለተጨቆነው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ ብሔራዊና ማኅበረሰባዊ ዓላማዎችን ይዘው መሠረታዊ ለውጥ (አብዮት) የማካሄድ ቅዱስ ኃላፊነት አለባቸው::

የተጠቆሙት ላብአደሮችና ድሀ ገበሬዎች የሚያስተባብር ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛና ፖለቲካዊ ጭቆና ደርሶባቸው በተለያዩ ዘዴ የተቀሰመ ትግል በሚያደርጉበት በአሁኑ ጊዜ ለጭቁኑ ሕዝብ የሚቆረቆሩ ተራማጆች ትግሉን የመምራትና አብዮታዊ መስመሩን የማስያዝ ታሪካዊ ግዴታ አለባቸው:: በዚህም አቀፍ እንቅስቃሴያቸውና በትክክለኛው መታደራሻ መንግሥት በመካሄድ ላይ ያለው ጠንካራ ለውጥ ምክንያት ሊደርስ የቻለው የጋራ ጭቆና ሊጠፋ የሚችለው በተደራጀ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ የተደራጀ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ በማርክሳዊ–ሌኒናዊ በሆነ ርዕዮተ–ዓለምና በማያቋርጥ አስተሳሰብ የሚመራ አብዮታዊ ድርጅት ያስፈልጋል::

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የምርት ግንኙነት

መደገፍ ብዝበዛ ከማስከተሉም በላይ የብሔሮች ጭቆና እንዲኖር አድርጓል። ስለዚህ ፋሽስታዊው ወታደራዊ መንግሥት የሚያደርገው ንኡስ-ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ ካለመቀበሉ፣ የብሔረተኝነቱ ሕዝብ ነፃነት የሚገኘው በትጥቅ ትግል ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣ ታሪካዊ ግዴታን ለመፈጸም ተ.ሐ.ህ.ት. ተብሎ የሚጠራ ብሔራዊ አብዮታዊ ግንባር አቋቋመ። ይህም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት [አ.ዲ.አ.] ወይም በሕዝባዊ አብዮት ጊዜ የሚካሄድ ሃቀኛ ብሔራዊ ትግል በመሠረቱ መደገፍ ትግል መሆኑን በማመን ነው።

ስለዚህ -

ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ትክክለኛ ሳይንሳዊ የላብ-አደር ርዕዮተ-ዓለም መሆኑን በማመንና በአሁኑ ጊዜ የሚካሄደው አብዮት ከግቡ ሊደርስ የሚችለው ይህንን መመሪያ በማድረግ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ:-

ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በማስተዋልና ለዓላማችን መቃናት ከሁሉ ፈር መሆኑን በመገንዘብ፣ ፀረ-ንኡስ ከበርቴያዊ ፋሽስትነት፣ ፀረ-ብሔራዊ ጭቆናና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም



የሆነ ፓርቲያዊ አቋም በመያዝ:-

ባገር ውስጥ በተደረገው ጠጋኝ ለውጥ ንኡስ-ከበርቴያዊ ፋሽስትነት ከዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በመተባበር የሰነዘረውን የብሔሮች ጭቆና ስንገነዘብና ጭቆናውም እንደሚያደርገን በማስተዋል:-

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች እንደሌሎቹ የሶስተኛው ዓለም ሃገሮች ሕዝቦች በዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና በየሀገሩ ባሉት አድሃሪያን (<u>በኢትዮጵያ በንኡስ-ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ ፋሽስትነት</u>) የተበዘበዙና የተጨቆኑ መሆናቸውን በመገንዘብ፤ ጭቆናና ብዝበዛው ሊጠፋ የሚችለው የላብ-አደሮችና የድሀ ገበሬዎች መደራጀት ተደራጅተውም ወዝ-አደሩ የሚመራው ተደጋጋሚ ታሪካዊ ተልእኮውን በመያዝ የፓርቲ ትግሉን አካሂዶ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በማካሄድ ብቻ ነው። ወዝ-አደሩንና ድሀ ገበሬውን ለማደራጀት በኢትዮጵያ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ የሆነ የፓርቲ ማሕበር መቋቋም የግድ ያስፈልጋል። ይህ የፓርቲ ማሕበር በመላው ኢትዮጵያ የሚደረገውን የፓርቲ ትግል በመምራት [ብሔራዊ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ኃይል

[ካሉት ብሔሮች በስተቀር] በአሁኑ ጊዜ የትጥቅ ትግል ለማድረግ ጎሬ ካሉት ሞቀን ብሔሮች ትግል ጋር በመተባበር ድልን አግኝቶ መደባዊ ብዝበዛና ብሔራዊ ጭቆና ለማጥፋት የዲሞክራሲና የሕብረተሰብአዊነት መሠረት ሊጥል ብቻ መሆኑን በመረዳት፡—

ቢሆንም ባለንበት ዘመን የነበረውን የብሔሮች ሁኔታ እየተባባሰ በመሄድ እነዚህ ብሔሮች ተባብረው ባንድነት እንዳይታገሉ ማድረግ በጣም አስቸጋሪና የማያስችል ሆኖ ይገኛል። ይህ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ስሜት [በተለይ በብሔረ-ትግሬ] የመደብን ንቃት ሸፍኖት ተገኝቷል። ይህ ስለሆነ የቻለው ጠንካራ ተጨቋኝ ብሔሮች ለብዙ ዘመናት በሃገሪቱ ተባብረው እንዲኖሩ በመደረጋቸው የተጨቆኑት ብሔሮች ጭቆናውን ሊሸከሙት አልቻሉም፤ ከእንግዲህ ወዲህም ተገደው በህብረት መኖር የማይችሉበት ተጨባጭ ሁኔታ የማይፈቅድላቸው ቢሆንም እንደ ገባው የህብረት መሰረት የህብረት ትግል ለማድረግ ህልዎና የትግሉን ሁኔታዎች ምክንያት መሆኑን በመገንዘብ፡— ┐



በተጨማሪ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ የተጨቆነና የተበዘበዘ በመሆኑ ለዲሞክራሲ ፀረ-ብሔራዊ ተፅዕኖዎች ፀረ-ንኡስ-ከበርቴያዊ ጠላቶቹ ለውጥ፡ እንዲያደርጉም ፀረ-ኢምፔርያሊዝም የሆነ አቋም በመያዙ ብሔራዊ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ዝግጁ መሆኑን ለማመን ነው።

የትግሉ ዓላማ መደባዊ ትግል ሆኖ ባሕሪው ግን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ነው። ይህ አብዮት የትግሉ መጨረሻ ሳይሆን ወደ ሕብረተሰብአዊነት መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ ለሕብረተሰብአዊነት የሚያስፈልጉትን ማቴሪያላዊ ሁኔታዎች እንደሚያሟላ የሚያደርግ አብዮት ነው። ትግሉም ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ከማንም አቋሙና ከአገር ውስጥ ተራማጅ ድርጅቶች ጋር የሚተባበር አብዮታዊ እንቅስቃሴዎችን የሚደግፍ መሆኑን እየገለፅን፡—

የሕዝባችን ተቃርኖዎች እንደዚህ በመሆናቸው በዚህ በተ.ሓ.ህ.ት. ሥር ተደራጅተን የሕዝባችንን ትግል ለማነቃቃትና ታሪካዊ መሰረቱን ለማስያዝ የትግላችንን ፕሮግራም አቀጣጥለናል።

ተ.ሓ.ህ.ት.

—o—

## የተ.ሓ.ህ.ት. ትግል መነሻው ፡ ባሕሪውና ዓላማው የሚመለከት ተጨማሪ ማብራሪያ፡-

### I ትግሉ ሲነሳው ሁኔታ፡-

#### 1. ፓለቲካዊ ሁኔታዎች፡-

ሀ. ፓለቲካዊ ሥልጣን. ለረጅም ጊዜ በቆየው የገባባታዊና የኢምፐርያሊስቶች ሥርዓት ባስከተለው ፓለቲካዊ ጭቆናና ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ ምክንያት ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝቦች በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም. አብዮታዊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ በተከፈቱ የትግል ዘዴዎች [ሥራ በማቆም የተቃውሞ ሰልፍ ወ.ዘ.ተ. በማድረግ] የደረሰባቸውን ግፍና በደል በግልጽ አሳታወቁ። ለተፈጠረው አብዮታዊ ሁኔታ መነሻ የሆነው የገዢው ጅግሮች በኤርትራ የተፈጠረው ፓለቲካዊና ወታደራዊ ሁኔታ እየከፋ መሄድ ፣ በብዙ ቦታዎች የረኀብ መስፋፋትና በችግሩም ምክንያት የብዙ ሕዝቦች ሕይወት መጥፋት ፣ የቤንዚን የዕቃዎችና የኑሮ ዋጋ መናር ሲሆን መሠረታዊ መነሻው ግን የመሬት ይዞታው ሥርዓትና የመንግሥት የኢኮኖሚ ውድቀት እንደዚሁም የመደቦች ቅራኔ መክረርና



መሠረታዊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ስለሌሉ መነሻ ነበሩ። እንቅስቃሴው አቋሙ ፀረ-ገባባታዊ ሥርዓትና ፀረ-ኢምፐርያሊዝም ሆኖ ስለዲሞክራሲ ስለሕብረተሰብ ፍትሕና ለኢኮኖሚያዊ ግስጋሴ የቆመ ነበር። ጭቁን መደቦች በሰላም ለመታገል በቀረቡበትና በተንቀሳቀሱበት በዚሁ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩ ከበርቴው መደብ ግንባር ቀደም ፓለቲካዊ ተሳትፎ ነበረው። የእንቅስቃሴው መልክ ከበርቴያዊ መስሎ በትግሉ ሰላማዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ግን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ባሕሪይ ይዞ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ እንቅስቃሴ ከነበረው ሁኔታ ጋር የተያያዙ ሁለት አበይት ጉድለቶች ነበሩት።

### II ኛ የፓለቲካ ድርጅቶች አለመኖር

በማንኛውም አብዮት እንደታየው ጭቁን ሕዝቦች በሚገባ ታግለው ለማሸነፍ በመጀመሪያ መደራጀት አለባቸው። ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ግን ምንም እንኳን በጨቋኙ ፀረ-ገባባታዊ ሥርዓትና ፀረ-ኢምፐርያሊዝም በሆነ መሰመር ቢታገሉም ትግላቸው ከግቡ ለማድረስ ፓለቲካዊ መመሪያና ትክክለኛ የትግል መስመር እንዲኖራቸው የሚያደርግ አብዮታዊ

ድርጅት አልነበሩትም። ያለ አብዮታዊ ድርጅት ደግሞ
አብዮታዊ ትግል ተካሂዶ ከግቡ እንደማይደርስ የታወቀ ነው።

፲፪ የመሰፍናዊ ቡድኖች መተናነቅና የንጉሡ ቃል

በዚህ ጊዜ ሕዝባዊው ትግል እያደገ የሚቀጥሉ
ሕዝብ መደገፍ ቀርቶም ጠባቂ በመምሰል የተነሳሳ አንድ
የፊውዳሉ ቡድን ተቋቋመ። ቡድኑ ከወታደራዊ ባለሥልጣናት
ጋር የመንግሥቱ ሥልጣን ለመካፈል ከንጉሡ ጋር ተስማምቶ ---
ለምሳሌ ብዙ ተሰሩዎች በዚህ መንገድ በንጉሡ ቃል ተደግፎ
በአዋጅ ለሕዝብ ተነገረ። ይህም የሕዝቡን መነሳሳት ለጊዜው
እንዲበርድ አደረገው።

፲፫. በዚህ እንዲሁ ሕዝባዊውና እንቅስቃሴ በሰላማዊ
መንገድ "እመልሰዋለሁ" ባይ "የምርኛ መኳንንት" ደርግ ተቋ
ቋመ። ደርግ ሕዝቡን በማደናገር ለሕዝቡ የቆመ መስሎ
ባዶ የተስፋ ቃል በመስጠት ጥሩ በቀለ በሚቀጥን የእንግ
ቁጊ ሕዝቦች ሰላም የፖለቲካውን ሥልጣን ጨበጠ። ደርግ
የፖለቲካ ሥልጣኑን የያዘው ሕዝቡ በሃገሩ ምድርዋም ዲሞክራ
ሲያዊ ባሰመረው ጊዜ ለሰሆነ በአብዮታዊያንና በፀረ-
አብዮታዊያን መካከል ትግል ጠንክሮ ተጀመረ።



የምርኛ መኳንንት መንግሥት ፀረ-አብዮታዊ በባህርያቸው ዓይነ
ተስፋዎችን እየሰጠ ሉአላዊ አዋጅን አውጆ ደርግ
ዊ ጥያቄዎችን እየፈታ እንደሚሄድ ሰዳ ሃሳ ምሁራንን
ወጣት መሳደብችም ሰይፉና ሥልጣን እየያዘ እንደሚ
ጊዜ ሉአላዊ ጠባቂን እያጋለጠ ሄደ።

ሉአላዊ ጠባቂን ለመተካት ሕዝቡ አንድ የሕዝቡን
ትግል ለማደናቀፍ ሀብረተሰብዓዊነት መመሪያው አስመስሎ
"ሀብረተሰብዓዊ" አዋጅን የመሬት ይዞታንና ትርፍ ቤቶችን
በሚመለከት ጉዳይ አወጣ። ይህ ደግሞ ምክንያት አዋጅ
ሥራ ላይ ለማዋል በቅድሚያ መሟላት የሚገባቸው
ነገሮች በመሟላታቸውና የአዋጁ መንፈስ አብዮታዊ መንገድ
የተካሄደ ሳይሆን የሕዝቡን ተቃውሞና የራሱ የአገዛዝ
ውድቀቱ ለመወጣት የተጠነሰሰ ፓለቲካዊ ስራ በመሆኑ
ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በደርጉ ውስጥ በቡድን የተከፋፈል
በሰልጣን ሽሚያ መተናነቅ መድረክ ሆኖ ነበር እየሆነ መጣ።
በቡድኖች መካከል ያለው ቅራኔና የሥልጣን ሽሚያ አሁንም
መፍትሔ ያልተገኘለት ነው። ሉአላዊ ደርግ እየሄደንና ተሸካሚዎችን
እያሰረ አንዱ ሌላውን ወንጀል የሠራ ለሁሉም

አንድ ዓይነት ድርድር በመስጠት በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ፋሽስት መሆኑን አስመስክሯል።

ለ- <u>የፓርቲን ነፃነት አስመልክቶ፡-</u>

በህብረተሰባችን መደቦች አሰላለፍ ድረስ ሃቀኛና ትክክለኛ የሆነ ነፃነትና እኩልነት ሊኖር እንደማይችል አያጠራጥርም። ይሁን እንጂ ጭቁን ሕዝቦች አብዮታዊ ትግላቸውን ለማካሄድ ሁኔታው የሚፈቅድላቸው የፓርቲ ነፃነት ማለት የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብና የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግና የመደራጀት መብት ሊሰጣቸው ይገባል። እነዚህ መብቶች ለሕዝብ መስጠት የሚችለው በሕዝብ ለሕዝብ የቆመ የዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ብቻ ነው። ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተራማጅ ወገኖች ትኩረታቸውን ደርግን ለመጣል በሚያደርጉት ትግል ወደ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሚያሸጋግራቸውን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ደጋግመው የሚጠይቁት። ይህ ጥያቄ ምንም እንኳ ጠንካራ ትግልና ረጅም ጊዜ የሚያስፈልገው ቢሆንም ታሪካዊ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ጭቁን ሕዝቦች ካደረጉ ቀርተው የፓርቲ



ሥልጣን ለመያዝ በማይችሉበት ጊዜ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት በማቋቋም ሥልጣን ወደ ሌሎች አድሃሪያን ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች እንዳይተላለፍ ሊከላከሉ ይችላሉ። በ1905 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በሩሲያ የተካሄደው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ምሳሌ ብንወስድ በዚያን ጊዜ በሩሲያ ውስጥ የነበረው ተራማጅ የፓርቲ ድርጅት የሰጠው ትንተና ያለውን ፡ የፓርቲ መመሪያ ፡ መሰረት ሊሆን ይችላል። መመሪያውም የጉልበት አደሩን ጥቅም ለማስገኘትና ለሶሻሊስት ሰፊው አብዮት በላይ የሆነ የፓርቲ ነፃነት ለሚያስፈልገው

ከዚህም አምባገነናዊው መንግሥት በዲሞክራሲያዊ መንግሥት መለወጥ ለአስቸጋሪነቱ፣ ይህ ለማድረግ የሚችለው ደግሞ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አዲሱ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት ከቋቋመ በኋላ መንግሥቱ በጊዜው ህዝባዊ ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ የአብዮቱ አካሄድና የጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት አስፈላጊነት በመመስከራት ጉዳይ ለህዝብ በደ ገለጻ ማድረግ አስፈላጊ ነው። መንግሥት የጉልበት አደሩ

መጻብ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄዎች በትክክል ገና ሥራ
ላይ እንደሚውሉ ያደርጋል።" ይገልፃል።

ይህ ሀሳባዊ አባባላቸው መንግሥት ለአብዮቱና ጭቁን ህዝቦች በነፃነትም ጥያቄው አሁንም መልስ ያገኘ የለውም ወደፊት ሆኖ ቀርቷል።

ሐ. በሶሻሊዝም ተፅዕኖ ሥር ያሉ ሀገራት ደርግ ተራማጆች ቢሆንም።
የብሔሮች ጥያቄ በሚከተለው መንገድ ያፈታል።

"የብሔሮች የራስ ዕድል ሥራ መወሰን ማለት ተጨቋኝ ብሔር ከጨቋኙ ብሔር የፖለቲካ መገንጠል አድርጎ ነፃ የሆነ የራሱ መንግሥት ማቋቋምም ማለት ነው። የራስን ዕድል ሥራ የመወሰን መብት የሚፈልጉትን መገንጠልን ያጠቃልላል። ብሎ መውሰን የመፈለግ መብት የሚያስገኝ በተሰጠ እንደሆነ ያገኙ ብሎ እንደመገንጠል የሚቃወሙ የሚመጣባቸው የምኒሊክ አገዛዝ ነው። ከዐፄ ተመልሶም ጭቁን ህዝብ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሥርዓት፤ የፖለቲካ አገር ሰፊ ገበያ ጥቅም በሚገባ ያውቃታል። ስለዚህ ወደ

ተሓህት 7

መገንጠል የሚያመራት ብሔራዊ ተፅዕኖ በሚከተለው ሁኔታዎች ቀጥሎ ምክንያት በአንድነት መኖር በሚፈልጉ የማይቻል ሲሆን ወይም ሆኖ ሲገኝና የኢኮኖሚ መተሳሰር አንድነት ሲከለከል ሆነ ወይም ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ የአብዮቱን አንድነትና የመደቦች ትግል ነፃነት በበለጠ ለማጎልበት የሚቻል ሲሆን በመገንጠል ብቻ ነው። የራስን ዕድል ራስን የመወሰን መብት መገንጠል ማለት የጨቋኙን ብሔር ጥቅም መጠበቅ ማለት ነው።

ሌኒን

በተጨማሪም ሌኒን የመገንጠል አስፈላጊነት ሲገልፅ፦

"የሕብረተሰብ መደብ መከፋፈል ለማጥፋት የተጨቋኙ መደብ አምባገነንነት እንደሚያስፈልግ ሁሉ የማይቀረው የብሔሮች መዋሃድ ሊገኝ የሚችለው መሸጋገሪያ በሆነው የብሔሮች ነፃነት፣ ማለት የብሔሮች መገንጠል መብት ሙሉ በሙሉ ሲኖር ብቻ ነው።" ይላል።

እንግዲያውስ በዚህ መልክ የአማራ ብሔር በትግራይ ሕዝብ ላይ የምታደርገው ተፅዕኖ እንደመለከትነው በኢትዮጵያ ያሉት ጭቁን ብሔሮች በተለይ ብሔረ-ትግራይ በጨቋኙ የአማራ ብሔር የሚደርስባቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ ወደ ጊዜ

ተሓህት 8

እየሆነና እየተባባሰ በመሄዱ በብሄሮች መካከል አለመተማ
መንና መጠራጠርን አስከትሎአል። ይህ በመሆኑ የኢትዮጵያ
ጭቁን ሕዝቦች በሙሉ በአንድነት ሆነው መደገፍ ትግልን
ለማካሄድ ከማያስችሉበት ደረጃ ደርሷል። በተለይ በየጊዜው
እየከረረና እየተባባሰ በመሄድ ላይ ባለው የብሄሮች ጭቆና
ምክንያት የጨቋኙና የተጨቋኙ ብሄሮች ሰራተኞች በዚህ
ጉዳይ ላይ አስፈላጊ የሆነ ውይይት፣ መረዳዳት፣ ሃቀኛና
ጠንካራ የሆነ አንድ ዓይነት አቋም ሊይዙ አልቻሉም።
ይህ ሊሆን የቻለው የብሄረ አማራ ሰራተኞች ትምክህተኞችና
አድርባዮች ሆነው ስለቀሩ ነው። በተራማጆች መካከልና
በጭቁን ህዝቦች መካከል ያለው መለያየት ለመንግሥቱ ጥሩ
አጋጣሚ ሆነለት እድሜውን እንዲያራዝም ረድቶታል።
ለዚህ ጭቁን ብሄሮች ከብሔራዊ ተፅዕኖ ነፃነታቸውም
ዓይነት ብዝበዛ ነፃ ለመውጣት መደበኛ መሆን ያለው
ብሔራዊ የትጥቅ ትግል ማድረግ ሃቀኛ ትክክለኛ ሆኖ
እናገኘዋለን። ብሔራዊ-ትግሉንም ጭቁን ብሔር በመሆን
ከነዚ የተጋለጠው የአርነት መንገድ መርጠዋል።



መ- ፕሮፓጋንዳ፦ ትላልቅ ብቻ ያለሉ ፍሬ ቢስ ባዶ አዋጆችና
መግለጫዎች በየጊዜው ይለፈፋሉ። እነዚህ ከእውነት የራቁ
መግለጫዎችና ቅጥፈቶች በመገናኛ መስመሮች በጭቁን
ህዝብና በሀገር ሰላም ይታወጃሉ። የአዋጆቹ ዓላማ
የህዝቡን አስተሳሰብ ለማደናገርና ወታደራዊ ደርግ በዚሁ
ለጠንካራ ለመቆየት ያለው ፍላጎት እንዲሁም ቡድናዊ
ጥቅም ለመጠበቅ ሆነ ተብሎ የሚደረግ የፕሮፓ
ጋንዳ ነው። ፋሽስታዊው መንግሥት የኢኮኖሚ ውድቀት
ሊደጋግመው ችግሩን ለመወጣት ፋብሪካዎችና ኩባንያ
ዎችንና የከተማ ቤቶችን እንዲሁም ግዛቶችን በቁጥጥሩ
ሥር የሚያደርግ አዋጅ አወጀ። በኤርትራ ውስጥ
በሚደረገው ጦርነትና በኢትዮጵያም ውስጥ በሚደረገው
ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ደርጉ ፋሽስታዊ ተግባሩን
ለማካሄድ ገንዘብ ስላጣው የግብር አዋጅና የሕዝብን
ንብረት በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል። ከዚህም በላይ
የሕዝቡ ፖለቲካዊ ተቃውሞ በርትቶ መንግሥቱን ለሰደ
ጋው ፋሽስታዊ አዋጆችን ያውጃል። በተጨማሪም
የህዝቡ ተቃውሞ ጠንክሮ የመንግሥቱ አቋም በመዳከሙ

ጊዜ ሕዝቡን በማታለል አንዳንድ መሬትና አዋጆችን ያወጣል
ፋሽስታዊ ጠባዩ እየተጋለጠ በሄደ ቁጥር ይህንን ጠባዩ
ለመሸፈን በግብር ሊገለፅ የማይችል የወረቀት አዋጅ
ያወጣል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን እነዚህ ባዶ
ፕሮፓጋንዳዎች ለጊዜው የህዝቡን አስተሳሰብ ሊጠመዝ
ዙ ቢችሉም በመጨረሻ የደርጉ ፋሽስትነትና አድሃሪ
ጠባዩ መገለጹ አልቀረም።

ቁጥር፡- ተራማጆችንና አድሃሪዎችን አንድ ዓይነት ክስ
እንዲቀርብባቸው በማድረግ አንድ ዓይነት ፍርድ እንዲቀ
በሉ ተደርጓል። በተጨማሪም 'ተራማጅ' አዋጆችን
ተቃውማችኋል በሚል ሰበብ ምክንያት ተራማጆችን ለማጥ
ፋት ፋሽስታዊው ደርግ የሚያደርገው ፀረ-አብዮታዊ
ድርጊት ለማንም ግልጽ ነው። ይህም ምንም እንኳ የሕዝ
ቡን የሀብና ፍርድ ለጊዜው ቢያወናብድም ውሎ አድሮ እውነተ
ኛ ገጽታው አልቀረም። የውሸት ፕሮፓጋንዳ የህዝቡን አስተያየት
ብዙ ጊዜ አወናብዶ ለማንደምደር የታወቀ ነው።
እንደዚያውም የደርጉ አድሃሪ ጠባይ በያለበት እየተጋለጠ
ሄዷል።



2. አስተዳደራዊ ሁኔታዎች

ሀ- የመሬት ይዞታው ሥርዓትና ችግሩ፡- በትግራይ
ውስጥ የመሬት ይዞታው ሥርዓት አብዛኛው መሰረታዊ
ርስት ነው። ርስት በቤተሰብ ይዞታ የሚካሄድ ትውልድ
ቆጥሮ ማለትም [illegible] የመሬት ይዞታ ሥርዓት ሰለሆነ በዚህ
መንገድ የጋራ ይዞታ ነው ለማለት ይቻላል። ከጠቅላላው
ህዝብ ዘጠና ከመቶ የሚሆነው ዕከታዊ ተብሎ ሙሉ
በሙሉ በርሻ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ መሬት ተከፋፍሎ
ተቆርሶ ይገኛል። እንደዚሁም የግል መሬትና ገለት አለ።
ይህ ቢሆን ግን ችግር መፍትሄ እንደሌገኝ በመጀመሪያ
መረዳት የሚያስፈልግ ነገር አለ። ይህም በትግራይ ውስጥ
መሬት እርሻ ከመኖር ብቻ ሳይሆን በደበልም የተወገደ
ት ምልክት ስለሆነ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ዋጋ
ከፍ ያለ መሆኑን ነው። ስለዚህ የመሬት ይዞታው
ሥርዓት ለመለወጥ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የመሬት
ይዞታ ለውጥ የሚያስፈልግ መሆኑን ማስተማርና
ማስረዳት በቅድሚያ መደረግ ካለባቸው አበይት
ጉዳዮች አንዱ ነው። እንደዚሁም የገበሬዎች የፓለቲካ

ፍላጎት እንደምለቻውና የወደቀ ጦንታቸውን ተጋብረው እንደመከተ ማደረጃት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በከተማና በገጠር ያለው የሥራ አጦት ችግር ለማቃለል የገጠር እንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ከርሻ መሳሪያዎችን መግዣና ማስፋፊያ መንግሥት የገንዘብ ማቶቤል እርዳታ ማሻሻል በተደመደ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቀዳሚ ነገሮች ሳይፈጸሙ ማንኛውም እቅድ መፍትሔ ሊሆን አያችልም። ደርግ እነዚህነገሮች ሳያሟላ በእቅድ ሃይል ለመጠቀምበመፈለጉ የነበረው ችግር እንዲባባስ አድርጎታል። ይህ ተግባር ሂደውን ያለተካተሉና ደርግ ፋሽስታዊ ጠባዩን ለመሸፈን ሆነ ብሎ ያደረገው ነው። ለዚህ የደርግ መንግሥት መንኮታኮትና ሥልጣን ወደ ህዝብ ማስተላለፍ የግድ አስፈላጊ ተግባር ሆኖ ይገኛል።

ለ- የኢንዱስትሪዎች እንቅስቃሴ

ትግራይ ጥቂት ብቻ በመሆንዋ በመንግሥት የተደገፉ ወይም በግል የተያዙ እንዱስትሪ ወይም ፋብሪካ ሊኖሩት አልቻሉም። እንዱስትሪዎች አዲስ አበባ ውስጥ [የጨርቃጨርቅ ብረታ ዋና ከተማ] ተከማችተው ይገኛሉ።



በዚህ ምክንያት የከተሞችን ከለመስፋፋትና የጉብ-አደሮችን ቁጥር ማነስ በግልፅ ይታያል። የኢኮኖሚ እድገትና የህብረተሰቡ ንቃት ከፍ እንዲያል አድርጎታል። ለእንዱስትሪዎች አለመስፋፋት ምክንያት የሆነው የመንግሥት መመሪያ አድሎዊ ለሆነ ነው። የትግራይ ሕዝብ ከዐዊ ያገኘውን እንስታቹ ገቢ ከፍተኛ ግብር ቢከፍልም ለእንዱስትሪዎች ማስፋፊያ የተደረገለት የመንግሥት ድጋፍ የለም። ባካባታዊ የሆነው የመሬት ይዞታ ሥርዓትም ለእንዱስትሪዎች አለመስፋፋት አንዱ ምክንያት ነው። በተጨማሪም ፋሽስታዊ መንግሥት ሥልጣን ላይ ለመቆየት ብዙ ገንዘብ ለወታደሮች መስጠት ስለሚፈልገው ከትግራይ ህዝብ ብዙ ገንዘብ በግብርም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ገፈፎ በመግፈፍም ላይ ነው።

3- ሕብረተሰባዊ ሁኔታዎች:-

ሀ- ጤና ጥበቃ (ጺ-ሁማናያሬሽን):- ከጥንት ወደ ጥንት እየተባባሰ የመጣው የኢኮኖሚ ብዝበዛ በሰፊው የትግራይ ህዝብ ላይ ድህነትን፣ረሃብንና በሽታን እየተደጋገመ እንዲደርስ አድርጓል። በተጨማሪም

የትግራይ ህዝብ ለረጅም ዘመን ሰብዓዊና ፓለቲካዊ መብቱ ተነፍጎ ሲጠቃና ሲናቅ እንዲሁም አድልዎ ሲፈጸምበት ቆይቷል። ይህም በደል ጨቋኝዋ የአማራ ብሔር ሆኖ ገዢ እንደመንግሥቱ መመሪያዋ አድርጋ ስትሰበስብ የቆየች ሲሆን ፋሽስታዊ ደርግም በባሰ በመልኩ መንገድ ቀጥሎበታል። ከዚህም የተነሳ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ኑሮው እንደቆራቆዘ ተደርጓል። በዚህ ምክንያት የሥራ ማጣት ችግር፣ ስርጭጭነትና ስደትን ከማስከተሉም በላይ ለሰን መጣና መንከራተት የትግራይ ሕዝብ ዕለታዊ ተግባሩ ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም ሕዝቡ ተጠርጣሪና የተጠላ እንዲሆን በመደረጉ በህብረት መኖር የማይችል ሆኖ ይገኛል።

ለ. የህብረተሰቡ ወደ ኋላ መቅረትና ዕረፍት ማጣት፡

ሰፊው የትግራይ ህዝብ ሥራ አጥቶ በስርጭጭነትና በስደት ወ.ዘ.ተ. ብቻ ሳይሆን በረሃብ፣ በድንቁርናና በበሽታ እየተሰቃየ ይኖራል። እነዚህም ችግሮች ወንጀል እንዲፈፀም ያገለግላል። ስትግሉ መሠረታዊ ምክንያት ኢምፔርያሊዝምና ገባርታዊ



ሥርዓት ይሁኑ እንጂ ጨቋኝዋ የአማራ ብሄር የገዥ ታደርገው የኢኮኖሚ ብዝበዛና የፓለቲካ ጭቆና ታክሎበት ነው። ከዚህም በላይ የሚያሳየው የህዝባችን ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ እንዲዳከምና ተዋክቦ እንዲጠፋ ወይም የአማራ ብሔር የገዢ መደብ ጥቅም እንዲጠበቅ የ፲፰ ዓመታት ታሪክና ባህሎቻችን በመጠቀሚያችንና መሞከሪያቸው ሆኖ ይገኛል። ይህ የታሪክ ሰርቆት በአንድ በኩል የአማራው ብሔር መሞከሪያ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ታሪክ እንደሌለው ሕዝብ እንዲያስቆጥረው የታቀደ የመንግሥት መመሪያ ነው። ቢሆንም የትግራይ ህዝብ ቋንቋውን ተቃውሞውን በቁጣና በጥንካሬ በብዙ መንገድ ደጋግሞ ገልጾታል። ይህና ይህንን የመሳሰሉ አድሃሪ ድርጊቶች አሁን ያለው ፋሽስታዊ መንግሥትም ስለቀጠለበት ሰብዓዊ ክብሩና መብቱ እስኪመለስ ድረስ ሰፊው የትግራይ ህዝብ ትግሉን አያቋርጥም። ጨቋኝዋ የአማራ ብሔርም ጭቆናዋ እስካላቆመች ድረስ ህብረተሰባዊ እረፍት አታገኝም።

## II መግቢያ:-

### ሀ- ብሔራዊ ትግል

ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ጭቆና እና በደል አስቆጥቶት ጭቆናውንና በደሉን ከሥሩ ለመንቀል የፖለቲካና የትጥቅ ትግል ሲያካሂድ ቆይቷል። በተለይም ከምኒልክ ዘመነመንግሥት ጀምሮ ፀረ-ሸዋዊ የመሳፍንቶች ሥርዓትና ፀረ-ብሔራዊ ተፅዕኖ የሆነ የተደጋገመ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አካሂዷል። ለምሳሌም በወያኔ ጊዜ ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ተጽእኖ ያካሄደው ዴሞክራሲያዊ የትጥቅ ትግል ምንጊዜም የማይረሳ ነው።

ስለዚህ:- ፩ አሁን ያለው አድሃሪ መንግሥት የብሔሮች ጥያቄ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ያለው አድሃሪ አቋም የነበሩትን የብሔሮች መብቶች እንደገፈፈና እንደካደ ስላደረገው:-

፪ እየተገፈፈ እየከረረ የሄደው የብሔሮች ጭቆና ጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔሮች በአንድ ዓላማ እንዲታገሉና መደባዊ ሥምረታቸውን እንዲያጠናክሩ ትልቅ እንቅፋት ስለሆነ:-



፫ኛ ምንጊዜም እንደኛ አብዮት ለማካሄድ መሰረት የሆኑ ጭቁን ህዝብ ተሳታፊ የሚሆኑበት የፖለቲካ ማህበር አለመኖሩ በሆነም 'ተራማጅ' ነን ባዮች የሸዋ ምሁራን ትምክህተኞችና አድርባዮች ሆነው ስለሚገኙ በአንድ የፖለቲካ ማህበር ሥር ተራማጅ ዓላማ ይዞ አብዮት ለማካሄድ የማይቻል ስለሆነ:-

ብሔራዊ ጭቆናና ተከታዩ አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝምን ለመታገል ጭቁን ብሔሮች መደባዊ ይዘታቸውን ያልለቀቀ አብዮት (ብሔራዊ የትጥቅ ትግል) ማካሄድ አለባቸውና ታሪካዊ ግዴታቸው ሆኖ ያገኙታል። ስለዚህ ነው ጭቁን የትግራይ ህዝብም አብዮታዊ ብሔራዊ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ያለው።

### ሀ- ዓላማውና ሥራው።

የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም እንዲሁም ፀረ-ንኡስ ከበርቴያዊ ወገኝ ለውጥ ነው። ስለዚህ የአብዮታዊው ትግል ዓላማ ከብሔራዊ ሥርዓትና ከኢምፔሪያሊዝም ነፃ የሆነ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ይሆናል።

ሀ- የአብዮቱ ጠባዮች፦ በመሠረቱ የአብዮቱ ጠባይ ፀረ-ባላባታዊ ሥርዓት፣ ፀረ-ንኡስ ከበርቴያዊ ጠጋኝ ከውጭ፣ ፀረ-ብሔራዊ ተጽእኖና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም ከመሆኑም በላይ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በመደገፍ ለዲሞክራሲና ለነፃነት የሚታገል አብዮት ነው። ባጭሩ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት [ኤን.ዲ.አር] ነው። የአብዮቱ መሠረታዊ ኃይሎችም ከድሀ ገበሬዎች፣ ከላብ-አደሮችና ከተቆርቋሪ ንኡስ-ከበርቴዎች እንደሁ-ም ከሌሎች ብሔራዊ ስሜት ካላቸው ክፍሎች ይመሠ-ረታሉ።

ትግሉ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በመሆኑ የአዲሱ ዲሞክራሲ ፕሮግራሞችን እንደ ፕሮግራሙ አድርጎ ተቀብሏቸዋል። ይህን በመመርኮዝ ተ.ሓ.ህ.ት. ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሕብረተሰባዊና ባህላዊ ዓላማዎችን እንደሚከተለው ይገልጻል።

በፖለቲካ፦— ፀረ-ባላባታዊ ሥርዓትና ፀረ-ኢምፔሪያ-ሊዝም የሆኑትን ኃይሎች በሙሉ የዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ያቋቁማሉ። መሠረታዊ የዲሞክራሲ መብቶች



ለጭቁን መደቦች ያለ ምንም ገደብ ይሰጣሉ። ህዝቡ በመንግሥቱ ሥልጣን ተሳታፊ እንዲሆን ተወካዮችን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ይመርጣል። ሥልጣንም የጭቁን መደቦች ይሆናል። ሕዝባዊው መንግሥቱ የሕዝቡ ድህንነት የመጠበቅና የመደብ ጠላቶችን የመርገጥ ኃላፊነት ይኖረዋል። ይህም ማለት ዲሞክራሲያዊ መንግሥቱም በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት [ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝም] የተመሠረተ የአስተዳደር ዘይቤ በመከተል የሕዝቡ ሙሉ ተወካይነት እንዲኖር የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የ[illegible]ብሄሮች ወ.ዘ.ተ. ልዩነት እንዳይኖር ማድረግ ማለት ነው።

በኢኮኖሚ፦- መሠረታዊ ሰለተ-ምርት ደምሰሰና የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ ከሥሩ ነቅሎ ነፃ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ማቋቋም የመሬት ይዞታውን ሥርዓት ማሻሻል ከበርቴያዊ ምርት ተቆጣጥሮ የምርት ኃይሎችን በህብረተሰቡ ቁጥጥር ሥር በማድረግ ለህብረተሰባዊነት ኢኮኖሚ መንገድ መጥረግና የህዝቡን ጥቅም ለማሟላት ማንኛውም ዓይነት ብዝበዛ የሌለበት የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት የተ.ሓ.ህ.ት. የማይታጠፉ ዓላማዎች

የቻው። ጊዜው ያለፈበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ባስከተለው ብዝበዛ ምክንያት በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉት መሠረታዊ ችግሮች፦ ድንቁርና፣ በሽታ፣ ድህነትና ረሃብ የመሳሰሉ እንዲሁም መደቦችና የመደብ ብዝበዛ ለማጥፋት ተ.ሓ.ህ.ት. የማያቋርጥ ትግል ታደርጋለች።

<u>በባህል</u>፦ አሁን ያለውን አሮጌና አድሃሪ ባህል ደምስሶ በአዲሱ ኢትዮጵያዊ ባህል መተካት የተ.ሓ.ህ.ት. ዓላማ ነው። ይህም ባህል ፀረ-ባላባትና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ባህል ከመሆኑም በላይ በመደብ ይዘታው የፆታና የንኡስ-ብሔሮች ልዩነት የሚያስከብር በላብ-አደር ዓለም-አቀፋዊነት ላይ የተመሠረተ የዕድገትና የእኩልነት ባህል ይሆናል።

ሰ- <u>የትጥቅ ትግል</u>፦ ከላይ የተገለጹት ዓላማዎችን በሥራ ለመተርጎም ትግሉ በማርክሳዊ-ሌኒናዊ-ማኦ-ሴቱንጋዊ ርዕዮተ-ዓለም የሚመራ ዘመናዊ የዱ:ፈጣ ውጊያ ታካሂዳለች ስትራቴጂ የተነሳ እንዲሁም ብሔራዊ መንግሥት ለማቋቋም የሚታገልም ብቸኛውን የትግራይ ሕዝብ የተጋድሎ የትጥቅ ትግል ሆኖ እናገኘዋለን።



## III <u>አሳሳቢ በሆኑት ውስጣዊና ዓለም-አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ ያለን አቋም።</u>

1. <u>የገጠር መሬት ጉዳይ</u>፦

የገጠር መሬት ጉዳይ በመላው ኢትዮጵያ አሳሳቢ የሆነ የኢኮኖሚ ችግር በመሆኑ በተለይ መፍትሔ ማግኘት አለበት። ችግሩ የሰፊውን ህዝብ ችግር በመሆኑ ለብዙ ጊዜ ተራማጆችን ሲያሳስብ የኖረ አሁንም ኢትዮጵያዊ መፍትሔ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው። ባላባታዊው የመሬት ይዞታ ሥርዓት ለጥቂቶቹ መሳፍንቶች ምቾት ሲሰጣቸው ለሰፊው ህዝብ ግን መከራን ድህነትንና ረሃብን አስከትሎአል። እንዲሁም ጭሰኛው ከእርሻ የሚያገኘው ገቢ እያነሰ በሄደ ቁጥር በዚህ አንፃር ደግሞ የሚከፍለው ግብር ከመጨመሩም በላይ በየጊዜው እየናረ የሚሄደው የዕቃዎች ዋጋ ኑሮው እየቆረቆዘ እንዲሄድ አድርጎታል። 'መሬት ላራሹ' የሚለው ዲሞክራሲያዊ የህዝብ መፈክር የመሬት ይዞታን ችግር መፍትሔ እንዲያገኝ የሚጠይቅ ነው። መፈክሩ ተደጋግሞ በህዝቡ ይጠቀስ እንጂ ችግሩ

እስካሁን ድረስ መሠረታዊ መፍትሔ አላገኘም።

ባካባቢያዊ ሆኖ በአምራች ላይ የተመሠረተው ሥርዓት የሚገኘው የመሬት ይዞታ ያስከተለው ችግር በትግራይ አሁን ያለው ሁኔታ በመመልከት መረዳት እንችላለን። መሬት በጊዜ ብዛት እየተቆራረጠ ለአንድ ሰው ወይም ቤተሰብ በተለያየ ቦታዎች ይሰጠዋል። የዚህ ዓይነት የመሬት ሥሪት ትርጉሙ በእርሻ ላይ በተመሠረተ ህዝብ ላይ ግልፅ የሆነ የእርሻ ችግር አስከትሏል።

እነዚህ በተገለጹት ምክንያቶች ተፈጥሮ ባስከተላቸው ችግሮች ከእርሻ የሚገኘው ገቢ እያደረ ሲቆረቆዝ የህዝቡ ብዛትና የሚከፍለው ግብር (ታክስ) ግን እያደገ ሲከ ሚጨምር ሕዝቡ በየጊዜው በረሃብ ይሰቃያል። በተጨማሪም በመሬት ክርክር ምክንያት በየፍርድ ቤት ይንከራተታል። ብዙ ሰውም አገሩን ለቆ ወደየከተማው ይሰደዳል። ከተማ ገብቶ ሥራ ስለማያገኝ ሴቶች ወደ ሸርሙጥና (ሴት አዳሪነት) ሲያመሩ ወንዶቹ ደግሞ ወደ ሌብነትና ማጅራት መቺነት ያመራሉ። የቀሩት ቀጥሎ ቸው ከ-እስከ ሊገልፅ የማይቻል ሰዎች በረሃብና በበሽታ



ያለቃሉ። ስለዚህ ይህንን ከባድ ችግር በምን ዓይነት መፍትሄ ሊገኝለት ይገባል? የሚለውን ጥያቄ ያጋጥመናል። ችግሩ በአብዮታዊ መንገድ መፍትሄ ሊያገኝለት የሚቻል ፕሮግራሙም ሁሉ ጎኑ የሚከተሉትን ሥራዎች ማካሄድን ይገባዋል።

1ኛ የገልተኝነት አከፋፈላዊ መሬት ማጥፋትና ባካባቢያዊ መልክ በመደራጀት እንዲደርሰው ማድረግ።

2ኛ ስለእርሻ ጥናት ደረጃ መንገድ መጥረግ። እነዚህ ሥራዎች መካሄድ ማለት ደግሞ ጭሰኛና ጉልተኝነት ማጥፋት፣ የመሬት ይዞታን ማስተካከል፣ የህብረት እርሻ ማስፋፋት፣ ጥቃቅን ወዘተ-ክዶር ማደራጀትና ዘመናዊ ትምህርት መስጠት ማለት ሆኖ እናገኘዋለን። በተጨማሪም የመሬት ክርክር ማጥፋት። በየገጠሩ የሚገኘው የሥራ ማጣት ችግር ማቃለል። በእርሻ ላይ የተመሠረተ ትንንሽ እንዱስትሪዎች ማቋቋም አስፈላጊ ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች እሥራ ላይ ለማዋል የሚቀጥሉት ነገሮች በአንድነት መሟላት አለባቸው።

1ኛ እስካሁን የፖለቲካ መብትና መመሪያ ከሰፊው ህዝብ የሚሰጥ፣ የሰፊው ህዝብ ጥቅም በእውነት የሚጠብቅ በጎብ-አደሩ የሚመራ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት

ማቋቋም።

2ኛ ፕሮግራሙ እየሠራ ካለ ለማግኘት የሚያስፈልገ የሰው፣ የገንዘብና ወይም ሌላ የማንኛውም ማቴሪያል ዝግጅት ማጠናቀቅ።

በዚህ አንፃር አድሃሪው <u>የንጉሠ-ነገሥቱ</u> <u>መንግሥት</u> ይህንን ችግር እንዴት ለማቃለል እንደሞከረ እንመርምር። መንግሥቱ በዚህ ረገድ ባደረጋቸው አዋጆች አንፃር ሰንመለከተው የመሬት ይዞታ ችግርንና ባሕረ-ሃሳባዊ መፍትሔው የገባው ይመስላል። ጠለቅ ብለን ስንመረምረው ግን መፍትሄው በወረቀት ብቻ ተወስኖ እንዲቀር የታሰበ መሆኑን እንገነዘባለን። ዋናው ቁምነገር ደግሞ ብሔራዊ መፍትሔው ማወቅ ብቻ ሳይሆን ችግሩን ለመፍታት አብዮታዊ ፍላጎትና ስሜት መኖሩ ነው። ይህ ማለትም አስፈላጊ የሆኑት ፓለቲካዊ፣ ድርጅታዊ፣ የገንዘብና የሰው ኃይል እና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማሟላት ነው።

አዋጆች ለ------

1. <u>ርስት</u>

ሀ. በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሚገኘው መሬት የባለሀብቶች



የሚያከማች ስለሆነ ለህዝቡ የመኖር ዋስትናና ክብርን ሳይሰጥ እንደቆየና አብዛኛው ህዝብ ከምግብ ጉድለ በእኩልነት እንደሚተዳደር ግልፅ ነው።

ለ- የኢትዮጵያ ህዝብ ሕብረትና ወንድማማችነት በበለጠ ለማጠናከር በኢትዮጵያ የሚገኘው የመሬት ይዞታ እንዲሻሻል ያስፈልጋል። በአስተዳደርም በኩል በሆነ ለአንድ አገር ህዝብ ተመሳሳይ ሕግ ማውጣት ጠቃሚ ነው። ይገባል።

ይህ ጉልታዊ ሥርዓት ለህዝቡ የመኖር ዋስትና ለጥቂቶች ብቻ ማወቅ ሥርዓት የፈጠረውን ግልፅ ድህነትና ረሃብ መከላከል ማለት ነው። ግልጽ የሆነ የመደብ ትግልና ልዩነት እያለ አብዛኛው ህዝብ በእኩልነት እንደሚተዳደር ግልፅ ነው ብሎ ማለት ችግሩን ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን መሠረቱ ለሆነው ህብረትና ወንድማማችነት ተብሎ ለተለያየ የመሬት ይዞታ ችግር አንድ ዓይነት አዋጅ ማውጣት መንግሥቱ ለማወናበድና ለማምበርበር የሚያደርገውን ሙከራ ግልፅ አድርጎ ያሳያል። ለችግሩም አብዮታዊ መፍትሄ ለማግኘት ስሜትና ፍላጎት እንደሌለው ያስረዳል።

2- የገበሬዎች ማሕበሮች በአዋጁ መሠረት ሥራና ዓላማቸው

እንደሚከተለው ተዘርዝሮ እናገኘዋለን።

ዓላማ ሀ- "በህብረተሰባዊ ፍልስፍና መሠረት የጭሰኞችና የድሀ ገበሬዎች ፓለቲካዊ መብትና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመጠበቅና ለማስፋፋት"

ለ- "ህብረተሰባዊነትን ሥራ ላይ ለማዋል በሚደረ-ጉት እርምጃዎች ተካፋይ እንዲሆኑ ከህብረተሰቡ ተራማጅ ክፍሎች በተለይም ከላብ-አደሩ ማህበሮች ጋር መተባበርና መተሳሰር።"

ሥራ ሀ- "መሬት የግል ይዞታ በሆነባቸው ቦታዎች ሁሉ መሬቱን በትክክልና ያለአንዳች አድልዎ ለጭሰኞችና ለድሀ ገበሬዎች ማደል።"

ለ- "በርስትና በዘመን መሬቶች ላይ አስፈላጊ የሆኑት የህብረት ሥራዎችና ድርጅቶች ማካሄድ።"

ሐ- ማደራጀት፣ ምርጫ ማካሄድ፣ ፓለቲካ ትምህርት መስጠት፣ የፓለቲካና የአስተዳደር ሥራዎች ማካሄድ የአካባ-ቢው ሕብረተሰባዊ ሕጋዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ማቃለል።"

ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሱትን አበይት ጉዳዮች



ለማካሄድ የተወሰኑ ድርጅቶች የተቋቋሙት በደንብ ባልተ ደራጀ መንገድ የፓለቲካ ንቃታቸው በጣም ዝቅተኛ በሆነ የሥራ ልምድ በሌላቸው ወታደሮችና በዘመቻው በማያምኑ ተማሪዎች እንዲሁም በአካባቢው ጭቃ ሹሞች ነው። መመሪያቸው የሚያገኙት ከዚህ ይባስ ብሎ ደግሞ ይህ የማደራጀትና ፓለቲካዊ ትምህርት የማካሄድ ሥራ የሚካ-ሄደው ጥቂት የአድሃሪው መንግሥት አባሎች 'ደርግ' ባወጡት መመሪያ መሠረት ነው። እነዚህ ጥቂት አወናባጆች ህብረተሰባዊነትን የሚያውቁት በቃል እንጂ በግብር ካለመሆኑም በላይ ይህ የሚያስፋፉ አውቀታቸውም ቢሆን ለማወናበድ እንጂ ቁምነገር ለመሥራት አይጠቀሙበትም። በተጨማሪ ደግሞ አድሃሪው ደርግ የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች ኮንፌዴሬሽን አውድሞ በምትኩ አድሃሪ የሆነ የላብ-አደሮች ማህበር እንደመሠረተ በማደራጀቱ የተባለው የሠራተኛው ማህበር መሠረት ነስቶት ይገኛል። ይህ የሚያሳየን እነዚህ የገበሬ ማህበሮች በወረቀት ላይ የሠፈረውን ዓላማና ሥራ በግብር ለመተርጎም ሳይሆን የተባለው ዓላማና ሥራ በወረቀት ላይ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር

የመንግሥት ወኪሎች ሆነው የመንግሥቱ ሥራዎችና ፍላጐት ለማሟላት መመሥረታቸው ነው። ስለዚህ የጭሰኞችና የደሀ ገበሬዎች የፓለቲካና የኤኮኖሚ ፍላጐት ለማሟላት አለመመሠረታቸውም ማለት ነው።

3- <u>ታጣቂ አርሻዎች</u>፦ አጥጋቢ ስለነዚህ አርሻዎች

ሀ- የመንግሥት እርሻዎችና የህብረት እርሻዎች እስኪደራጁ ድረስ መንግሥቱ እነዚህን ታጣቂ እርሻዎች በመሰለው መንገድ ያስተዳድራል። በተጨማሪም መንግሥት በመሰለው መንገድ እስኪያስተዳድራቸው ድረስ የእነዚህ ታጣቂ እርሻዎች ባለቤቶች ማስተዳደራቸውን ይቀጥላሉ።

ለ- በየመሥሪያ ቤት እንዲሰራም በተሰጠው መመሪያ መሠረት ደግሞ እነዚህን ታጣቂ እርሻዎች በመካፈል የሚሊ ልግ ገበሬዎች የሉም በሚል ምክንያት እነዚህ እርሻዎች ለባለቤቶቹ ወይም ለሌላው ሰው በኪራይ ሊሰጥ እንደሚችል እንገነዘባለን። በተጨማሪም የተወረሱት ታጣቂ እርሻዎች ያስተዳደርና የቴክኒክ ጉድለት ይፈጠራል በሚል ምክንያት በማህበር መንግሥታቸው ቀርቶ በመንግሥት ሥር እንዲተዳደሩ ተደርጓል።



መንግሥቱ ታጣቂ እርሻዎችን በመሰለው መንገድ ያስተዳድራል የሚለውን ሃሳብ በደርጉ አገዛዝ ስንመለከተው ደርጉ እነዚህን እርሻዎች ለኢምፔሪያሊስቶች በኮንሰሲዮን ለመስጠት እንደሚችል እንረዳለን። ስለዚህ አድሃሪው መንግሥት አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላትና ለማሟላትም ስለማይችል የመንግሥቱ መውደቁና በተፈላጊ መንግሥት መተካት አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን።

<u>የከተማ ቦታና የትርፍ ቤቶች ጥያቄ</u>

ያንገዳች ጥርጥር በሌለ ኢትዮጵያ የሚገኙት የከተማ ቦታዎችና ቤቶች በጥቂት መኳንንት፣ ከበርቴዎችና ቡችሎቻቸው እጅ ሥር ተይዘው ይገኛሉ። ስለዚህም የቤት ኪራይ፣ የከተማ ቦታ ዋጋና የቤት ማሠሪያ ዋጋ በየጊዜው ከመጠን በላይ እየናረ ስለሄደ በከተማው ሕዝብ ላይ ታላቅ ውድቀትን አስከትሏል። እንደዚሁም እነዚህ የገዢው መደብ አባሎች መጠን የሌለው የግል ንብረትና ከዚሁ የመነጩ መብቶች አግኝተዋል። ከግብር ነፃ ከመሆናቸውም በላይ ባስፈለጋቸው ጊዜ ያስፈልጋቸውን ኃይል በመጠቀም የፓለቲካ ሥልጣን አግኝተው ሕዝቡን

ከመርገጥና ከመበዝበዝ ተጠቃ መውበታል። በዚህ ምክንያት አብዛኛው የከተማ ህዝብ የከተማ ቤትና መሬት የማግኘት መብቱ ተነፍጎ በቤት ኪራይ ተሰቃይቷል። በዚህ ጊዜ ነው ለእንደዚህ ዓይነት ችግር አስፈላጊ፣ ትክክለኛና የማያዳግም መፍትሔ ሊፈለግ ለት የሚገባው፤ ይሁን እንጂ አድሃሪው መንግሥት ችግሩን በሕዝቡ ፍላጎት መሠረት በማጥናት ፋንታ ከጥቂት ገዢዎች ፍላጎትና ጸብመው አብዮታዊ ሰዎች ከፕሮፓጋንዳው ጥቅምም ብቻ አዋጁ በማወጅ ችግሩ እንዲስ ቀጥሏል። ይህንን ለማስት የቻልነውም:-

1ኛ መንግሥቱ ባወጣው አዋጅ ምክንያት የቤቶች ሥራ እንዲሰፋ መበረታታትና ይህም የእሱ ቶን የኢኮኖሚ ዕድገት ወደፊት የሚገፋት ሆኖ በመንግሥትና የቤቶች ሥራ እንዲስፋፋ በመንግሥት ወይም በሕዝቡ ማህበሮች የሚካሄድበትን መንገድ ተዘጋጅቶ ባለመቀየቱ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው የከተማ ቦታና ቤት በጥቂት ሰዎች እጅ በመኖሩ ይህንን ታላቅ ሥራ ለማካሄድ የመንግሥት ተካፋይነት አስፈላጊ ሊሆን ነው። ሆኖም መንግሥቱ በዚህ ረገድ ፈጽሞ አልተዘጋጀም።

2ኛ ይህ የቤቶች ሥራ መቋረጥ በቀጥታ ከሚመለከታቸው



ሠራተኞች [ግምበኞች] ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድም ለቤት ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎች በሚሠሩ ፋብሪካዎችና ድርጅቶች ውስጥ ያሉትንም ሠራተኞች የሥራ ማጣት ችግር አስከትሎባቸዋል። ከዚህ አልፎም በ1-2 ክፍል ቤት ውስጥ ይኖር የነበረው ቤተሰብ ከመንግሥቱ ጋር ባነሳው አልህ ምክንያት ጉ-ዩ ክፍሎችን ስለያዘ በየከተማው በብዛት ሺህ የሚቆጠር ህዝብ ኑሮውን በሆቴል ውስጥ መስርቶ ከድሮው በባሰ ቀጥ በሌለው ምዝመዛ ሲሰቃይ ይገኛል።

3ኛ ከጊዜ ወደጊዜ እየናረ በሚሄደው የዕቃዎች ዋጋ አንፃር ሲንመለከተው የቤት ኪራይ ለመቀነስ የተወሰደው እርምጃ የማያዳግም መፍትሔ ሳይሆን ጊዜያዊ እርግጠን ሆኖ አናገኘዋለን። ይህ የሚያሳዩን እንደዚህ ዓይነት የተደራረበና ከባድ ችግር ሊወገድ የሚችለው በአፍ አዋጅ ሳይሆን ከሰፊው ህዝብ የመነጨ የሰፊው ህዝብ መንግሥት ሲመሠረት ብቻ ነው።

## የኤርትራ ጥያቄ

የኤርትራ ጥያቄ መነሰሻው ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ መሠረታዊ መልስ ለመስጠት የሚከተሉትን ታሪካዊ መረጃዎች መመልከት

ያስፈልጋል።

ሀ- ሁለት ህዝቦች፣ ሀገሮች ወይም ብሄሮች በተለያየ ጊዜ የየራሳቸው አስተዳደር ይዘው ቆይተው አንዱ ግዛቱ ላይ የሚያደርገው በሃይል የተደገፈ ግዛት የቅኝ አገዛዝ ተግባር ነው።

ለ- እንዲሁም ሁለት ሀገሮች በሁለቱም ፈቃድና ፍላጎት የየግላቸው መብት ጠብቀው ከተባበሩ በኋላ አንደኛው ሌላውን ሊያጠፋ እርምጃው የቅኝ አገዛዝ እርምጃ ነው።

እንግዲ በተጠቀሰው ታሪካዊ ሃቅ መሠረት የኤርትራ ጉዳይ ስንመረምር የሚከተሉት ነገሮች ያጋጥሙናል።

ሀ- በ1890 ዓ.ም. አካባቢ ኤርትራና ኢትዮጵያ ለየብቻቸው የተለያየ አስተዳደር ይዘው ይኖሩ ነበር። ይኸውም ኤርትራ እንደ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ኢትዮጵያ ደግሞ እንደ አንድ ነፃ አገር ሆነው ይኖሩ ነበር።

ለ- በ1952 ዓ.ም. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን መተዳደር በጀመረችበት ጊዜ ሁለቱም ሀገሮች ያደረጉት ስምምነትና የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር መሆንዋን ይጠቅሳል።



ሐ- ይሁን እንጂ በ1962 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ የወሰደችው እርምጃ ስምምነቱን "አንደኛው ወገን ብቻ ከተባበሩት መንግሥታት ሳይጠይቅ ሊጥሰው አይችልም።" የሚለውን ሕግ በጣሰ የዐፄ ግዛት ሆኖ ይገኛል።

ስለዚህ ኤርትራ ውስጥ የሚደረገው ትግል ያንገዳች ጥርጥር ሃቀኛና ታሪካዊ መሠረት ያለው ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ነው።

## የኢትዮጵያ አብዮት

ሀ- በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ሁኔታዎች ስንመረምር ህዝባዊ አብዮት ከፀረ-አብዮታዊ ደርግ ጋር ብርቱ የትንንቅ ትግል በሀገሪቷ ላይ መሆኑን እንገነዘባለን። ንኡስ-ከበርቴያዊ ፋሽስታዊ ደርግ መላው የኢትዮጵያ የፓለቲካ ሥልጣን ጨብጦ ሕዝባዊ ተራማጆችን በጅምላ በመግደል ላይ ይገኛል። ህዝቡን ለመጨቆንና አብዮታዊ ለመምሰል ተንኮል ያዘሉ ብዙ አዋጆችን እያወጣ ፀረ-አብዮታዊነቱን ለመሸፈን ሞክሯል። ሆኖም ይህ ተንኮል ውሎ አድሮ በመጋለጡ ህዝቡ ከአብዮታዊ ግስጋሴው ፍንክች አላለም። ምክንያቱም የደርጉ ባዶ አዋጆች የሰፊውን ህዝብ አብዮት ጥያቄዎች ሊያሟሉ ስላልቻሉና

ሊመልሱም የማይችሉ ሰለሆነ ነው። የሰፊው ህዝብ ፍላጎት ሊሟላ የሚችለው በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ብቻ ነው። ሉ- ከዚህ የተመሰቃቀለ ኑሮ መውጫ በር ግልፅ ነው። ይኸውም የብሔሮች የትጥቅ ትግል ወይም በሀገሪ ኢትዮጵያ የሚካሄዱ ትግል ማካሄዳቸው ነው። የትኛውንመንገድ መከተል እንደሚገባ የሚያዘው ግን በየቦታው የሚገኘው ተጨባጭ ሁኔታ ነው። ሁለቱም መንገዶች የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አመራር ተከትለው ሳይንሳዊ ህብረተሰባዊነትን ለመገንባት ዓላማ አላቸው። እነዚህ ሁለት የትግል መንገዶች ተግባራዊ ሥራቸውን እንዳካሄዱ አብዮታዊያን ነገዶች የአምባገነን ብሔር ትምክህተኝነትና ጠባብ ብሄር ተኝነት ያጠቃቸው ሰዎች አግዳሚዎች ይገኙ። "ህብረተሰብ ዓዊነት ለባል" ከፋርን መተባበር ያሰፈልግል በማለት "ቀድሞ የነበረውን የመንግሥት ሰርዓት ሙሉ በሙሉ ባይወድም አዲስ ህብረተሰባዊ ሥርዓት መመሥረት አይቻልም።" የሚለውን ታሪካዊ ማርክሳዊ ሃቅ ይከዳሉ። የተለያዩ ብሔሮች አብረው በሆኑ ጊዜ ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ለታገሉ ይችላሉ በማለት በጊዜው ባለው



ተጨባጭ ሁኔታ ይስተዳደራሉ የአማራን ብሔር ጭቆና በሽፍንፍን ለማቆየት የቃለመ የትምክህተኞች ተንኮልደግሞ በሌላ በኩል ነዘሎ እነዚህ የአፍ ለቃውንት አወናጅነታቸው እንዳይነቃባቸው በታሪክ የተደገፉትን የብሔሮች ትግል በሰፊ ጠባብ ብሔርተኝነት ለማሳሰብ ይሞክራሉ። እንደዚህ ዓይነቱ አጉል መሰሪቆና ትምክህተኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊያደናቅፉና ሊያስቆርጡት ቢሞክሩም። በአሁኑ ጊዜ ሰፊው ህዝብ ተደራጅቶ አብዮት ለማካሄድ ገዢው ፊውዳሉ አዲስ ማደናበሪያና አጉል መሰሪቅ በህዝብ ላይ የተፈፀመ ታላቅ ታሪካዊ ክህደት ነው።

## ኢምፔሪያሊዝምና ሦስተኛው ዓለም

በዓለም አቀፍ አድሃሪነት ለአብዮታዊ ግስጋሴዎች እንቅፋት የሆነው ኢምፔሪያሊዝም የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦችን በአንድ አገር ለመግዛትና በመጨቆን ላይ ያለው በየአገሩ ካሉት ቡችሎች በመተባበር ነው። ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ የሚያካሂደው ግርዶሽ እየተባለ ከኢምፔሪያሊስት አገሮችና ከተዋዋሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች [የዓለም ባንክ] የዓለም የገንዘብ ድርጅት [አይ.ኤም.ኤፍ] በሚሰጠው የተሸፈነ

መርሁ አቋሙ በተዛባ የንግድ ልውውጥና ጥሬ ሀብቶችን ያለአግባብ በመዝረፍ ነው።

ፓለቲካዊ ጭቆናውም የሚያካሂደው በዓለም ዙሪያ ባቋቋማቸው ወታደራዊ ሠፈሮችና በውጭ ጉዳይ አመራሩ ነው። የሦስተኛው ዓለም ህዝቦች በኢምፔሪያሊዝምና በየአገሩ በሚገኙት ቡችሎች ላይ ግሁድ ጦርነት ካወጁ ቆይተዋል። የነዚህ ሕዝቦች ትግል በየቀኑና በየሰዓቱ ወደ ድል በመቃረብ ላይ መሆኑ የማያጠራጥር ነው። ካምቦዲያ፣ ጊኒ ቢሳዎ፣ ሞዛምቢክ፣ ቬትናም ወ.ዘ.ተ. በኢምፔሪያሊዝም ላይ ያገኙት ድል ኢምፔሪያሊስቶችን አዳክሟቸዋል። ይህ የኢምፔሪያሊዝም መዳከም ዓለም አቀፍ አብዮትና የህብረተሰብዓዊነት ድል ማለት ነው። የኛ ትግልም ከነዚህ ህዝቦች ትግል ሊነጠል የማይችል ተራማጅ ትግል በመሆኑ ከነዚሁ ጭቁን ህዝቦች ትግል ብዙ እንማራለን። የጋራ አጋሮቻችንም በማድረግ ህብረታችንን እንገልጽላቸዋለን።

<u>የውጭ ጉዳይ አመራር</u>

እስካሁን እንደተገለጸው ሁሉ እንቅስቃሴያችን የዓለም ህብረተሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች አካል ነው።



ስለሆነም ለዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ያለው ጠንካራ ተቃውሞና ከተራማጅ እንቅስቃሴዎች ያለው ድጋፍና ተባባሪነት ይገልጻል። በውጭ ጉዳይ አመራሩ የወዝ-አደር ዓለም አቀፋዊነት ይከተላል። ጠባብ ብሄርተኝነትና ትምክህተኝነት በጽኑ ይቃወማል።

ስለዚህ ተ.ሓ.ህ.ት

1- ካገኙዋቸው የፓለቲካ ተጽእኖ ከግል ሰቦች፣ ወይም ከማህበሮች እንደዚሁም አገሮች የሚሰጠውን ማንኛውም የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ በደስታ ይቀበላል።
2- ቅኝ አገዛዝ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝንና ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም ላይ የሚገኙትን አፍሪካዊያን ወንድሞችን መደገፍ ብቻ ሳይሆን ከነሱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ትግሉን ያካሂዳል።
3- ፅዮናዊያንና ኢምፔሪያሊስቶችን በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶችን በመቃወም ላይ ከሚገኙት ፍልስጤማዊያንና የዐረብ ህዝቦች ጋር ግኙነቱን ያጠነክራል።
4- የሮዴሽያንና የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ መንግሥታት

በጥብቅ ይወግዛል።

5. ከዲሞክራሲና ከህብረተሰብዓዊ ዕድገት በመታገል ላይ ከሚገኙት የላቲን አሜሪካና የኤስያ ህዝቦች ያልተቆጠበ የሞራል ድጋፉን ይሰጣል።

ፋሽሽታዊ ደርግ ይውደም!

ኢምፐርያሊዝም ይንኮታኮት!

ድምቀት ለዓለም ተራማጅ ሃይሎች!

የትግራይ ህዝብ ትግል ያሸንፋል!!

## ቅኑዕ ብሄራዊ ቃልሲ መደባዊ ቃልሲ እዩ፤

## Genuine National Struggle is in ESSENCE Class Struggle

ኣብ ጭቑናት ብሄራት ካብ ዝርከብ ህዝቢ ብዝኸፍአ ዝሳቐዩ ኣትዮም ዝምዝመዙ ርዒፀ- ብክልኣት ሓረስታትን ከምኡ'ውን ካልኦት ብሸቕሊ ዝናበሩን እዮም። ካብ'ዚ ድማ ብሄራዊ ጭቆና መደባዊ ጭቆና ምዃኑ ሰክዘርኛየና--- ኣንፃር ብሄራዊ ጭቆና ዝግበር ቃልሲ'ውን ኣንፃር መደባዊ ጭቆናን ኣንፃር መድሓርሓርትን መከሓዳትን ተወላዲ ናይ'ታ ብሄር ዝግበር ቃልሲ ምዃኑ ዘየጠራጥር ሓቂ እዩ።

Among the people of the oppressed nationalities, those who actually suffer are mainly the oppressed and exploited classes, the workers, peasants and other labouring classes. From this we can see that national oppression is in reality class oppression, and that the struggle against national oppression is in reality a struggle against class oppression, and often simultineously a struggle against the reactionaries and traitors of one's own nationality.

ተ.ሓ.ህ.ት.



ብሄራዊ ማዕርነትን ሙሉእ ናጽነትን ንምርካብ ውፁዕ ህዝቢ ትግራይ ብተ.ሓ.ህ.ት. ተሰሪዑ ዘዓሕክል ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ቃልሲ ብምክያድ ነቲ ኣስካሕኳሒ ዘሎ ብሄራዊ ጭቆና ሃፀያዊያን ማሕበር ኩሉኹሙ ገዝኣት ክጥፍኦ እዩ:: ከምኡ'ውን ሰደብ መግመዝትን እርጋት ዝምዝመዝን ክበሩ ንምብርካኽ ኣቲ ቃልሲ ናብ ዔሰዊ ቃልሲ ኣሰጋጊሩ ናይ ቀርነት ክታ ክንምንም'ዩ::

Inorder to achieve national equality and total emancipation, the oppressed people of Tigray nationality, under the guidance of T.P.L.F. will resolutely carryout national democratic revolution, put an end to the national oppression of the imperialists and overthrow the rule of their lackeys; they will then carry through the Socialist revolution and destroy all the exploiting classes and systems.

T.P.L.F.

—xxxoxxxoxxx—